# አመራር በኢትዮጵያ ፣ ዲሞክራሲያ በኤርትራ፣

# ዴሞክራሲያ በኤትዮጵያ

በአቦ አራዳ አባ ሻውል
ኅዳር ፭ ቀን ፪ሺህ ፮ ዓ.ም (5, 2006 ዓም)

## መግቢያ

የአመራር የዲሞክራሲና የዴሞክራሲያ ፅንሰ-ሐሳቦች ምን እንደሆኑ፣ ለምን እንደሚያስፈልጉ ከመወያየታችን በፊት ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ኤትዮጵያ ምን ማለት እንደሆነ ማሳወቅ አስፈላጊ ይሆናል።

ኢትዮጵያና ኤርትራ ማለት በቅኝ ገዥዎች አዕምሮ ተተምኖ በካርቶግራፊ ባለሞያ ተሸንሽኖ የተሰጠ ካርታዊ ችሮታ ነው ለማለት ያስደፍራል። ባለሞያዎች እንደነ አቶ ዘውገ ፋንታ ፣ እንደነ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ ማርያም የመሳሰሉ የጆግራፊ ምሁራን ቢያስረዱ ይመረጣል። ኤትዮጵያ የተባለው ኅብረተ-ሰብ - society - ግና ሁለቱንም አገሮች ኢትዮጵያና ኤርትራ የሚያጠቃልል ቦታና ሕዝብ የሠፈረበት ለማለት ነው። በሌላ ሥዕላዊ አነጋገር ኤርትራ ማለት በእኔ ቋንቋ ከዛላ አንበሳ-አሰብ-ቃሮራ ( The ZAK Triangle) ይለዋል የዲሞክራሲያ መጸሐፉ። ኢትዮጵያ ደግሞ ሞያለ-አፋር-ዛላአንበሳ-ኩርሙክ (The MAAK Rectangle) ይለዋል የለጋሹ መጸሐፍ።

ኤትዮጵያ የሚለው የወል ሥም ግና ሁለቱንም ያጠቃልላል ማለትም ዛክ-ማክ ( ZaK/Makk - triangle & rectangle) ተብሎ ይታወቅልኝ።

ኤትዮጵያ ለሚለው የጋራ ሥም የሕዝቡ ኑሮውና ዕምነቱ ብቻ ሳይሆን በአብዮቱ ምክንያት ደሙንና አጥንቱን የከሰከሰበት መዝሙርም ነው። ባሕላዊና ታሪካዊም ቅርስ አዘል ስለሆነም ጭምር ነው። ጦርነት፣ አብዮትና ሠላም መፎክሮች የኤትዮጵያን ሁኔታ ውስብስብ አድርገውታል። ፖለቲካ፣ አይዶሎጂና ጦርነት የቅደም-ተከተል (priority) ያስፈልጋቸዋል። የፖለቲካ አንድነት የሚመጣው ሁሉም ወገኖች በዲሞና ዴሞ ንድፈ-ሐሳብ ከተስማሙ በኋላ ነው። የፖለቲካ አንድነት ያለ ፖለቲካዊ ሥርአት አይሆንም።

ወደ ዋናው አርዕስት ጉዳይ ልግባና ጥንሰ ሐሳቦች ማለትም አመራር፣ ዲሞክራሲያና ዴሞክራሲያ በምን ምክንያት ነው በኢትዮጵያና በኤርትራ እልባት ያላገኙት? መሪዎቹ ተንኮለኞች ሆነው ነው? ወይስ ሕዝቡ ደደብ ሆኖ ይሆን? ወይንም የተማረው አካል የውሸት ትምህርት ስለቀመሰ በውጭ ኃይሎች ተታሎ ነው? የሚሉ መላ ምቶች አይኖሩም አይባልም። ይኖራሉ። ጉዳዩ ግና ሁሉም የተሳሳተ አመለካከት ቢሆንስ ነው?

ዋናው ሚሥጢሩ በአገራችን የትራንስፖርትና የመገናኛ መስመሮች ስለ አልተዘረጉ ፖለቲካዊ አመለካከት እና አሠራር ስለ አልነበረ ሊሆን አይችልም? ሌላ ችግር ደግሞ ሊያመጣ ይሆን?

አዎን በኢና በኤ ወይም E = E ልዩነትና አንድነት በTP እና በCR (Transportation & Communication) ችግር ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

ይህን አባባል እውነት ሊሆን የሚችለው ከ፲፱ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ነው። ማለትም እንዱስትሪያዊ ማምረቻዎች ሲስፋፉና ወደ ከተማ መጉረፍ (Industrialization, Manufacturing and Urbanization) መጉረፍ ሲጀመር ኤትዮጵያ ግና ራሱዋአን ችላ ሳትነካካ ሳይነስና ቴክኖሎጂ ሳትቀበል ኖራለች። በእኔ ዕይታ አያስፈልጋትም ነበር አሁንም አያስፈልጋትም ከሚሉ ወገን ነኝ። የኤትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ዓመታት ያካበተው ፈጠራንና ልምድ የፐና የር (Transport and Communication) ጉዳይ አሳክቶ፣ በደጋ፣ በቆላና በወይን አደጋ/ቆላ አስተካክለው ያስረከቡን አገር ነች። ይህ ሌላ አርዕስት ጉዳይ በመሆኑ ለሌላ ቀጠሮ ይሰጠኝ እላለሁ። እንዲያው ለግንዛቤ ያክል በአሲምባ ፍቅር የመጽሐፉ ሽፋን ላይ የተለያዩ ሦስት ዓይነት ገጽታ ያላቸው የተራራዎች ፎቶግራፍ መመልከት ይበጃል። ከላይ ካልነው ሥልጣኔ ይዛመድ ይሆን?

ለማነኛውም ችግሩ ችግር ነው ካልነው የመገናኛና የግኑኝነት (Communication & Relations) ጉዳይ ይሆናልና በትዕግሥት እንድንደማመጥ እጠይቃለሁ። ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም እንዲሉ የኢትዮጵያ “አብዮት” ይህንን አባባል አልተቀበለውም ነበር። ኢሕአፓና ኢሕአፓዎቹ የጉልቻው ጠቃሚነቱን ረስተው ሳይሆን ወጥና ጉልቻ ስለማይነጣጠሉ ነው ይኸን መፎከር ያነገበው። በBR/ብር Partnership ቀለል ባለ መግባቢያ አስፈላጊነቱ ይታያል። ሻለቃ፣ ማዘርና አቦ አራዳ ሻውል ጥረታቸው የሕዝብ ድልድይና መንገድ -Bridges & Roads (BR) መዘርጋት ብቻ ሳይሆን ሦስት እግር ያለው ጉልቻ ለመዘርጋትም ጭምር ነው።

## አመራር፣ በወል ወይ በግል

ስለ አመራር ሲወሳ ሁሌም የኢትዮጵያውያን ዋና ጥያቄ የሚሆነው መሪው ማነው? ሲሆን የኤርትሪዎች የጥያቄ መፍትሄ ደግሞ “ሱቅ ጥዑም” ነው ትርጉሙም ዝምታ ወርቅ ነው ለማለት ነው።ታጥቦ ጭቃ ማለት ይኸ ነው። አለ ጽነሰ-ሐሳብ ንድፈ-ሐሳብ የለምና ነው። የኤርትራ ፖለቲካዊ ትራጀዲ ከዚህ የመነጨ ይመስላል።

የኤትዮጵያውያን መልስ ግን “እኔው ራሴ” ይለዋል። እንግዲያውስ ለዚህ ነው ኢሕአፓ የተባለው ድርጅት መሪ ያጣው? ወይም የሌለው ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ብዙ መስዋዕት ተከፍሎበታል እየተከፈለበትም ይገኛል። ነገሩ የዲሞክራሲያ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዴሞክራሲያ ንድፈ ሐሳብ ይጨምራል። በፈረንጅ አነጋገር ትንሹ *-d-* እና ትልቁ *-D-* ይባላል። የኢሕአፓ ድኅረ-ገጾች ይህን የሚያመላክቱ ይመስላል ለተመራመረው አካል። የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን

የሁለቱም አገር ምሁራኖች በዲና በዴ ወይንም በትልቁ Dና በትንሹ d ያለውና ሊኖረው የሚችል ፌኖመና (phenomena) አይታያቸውም ወይንም አያውቁትም።

በኤትዮጵያ ትክክለኛውን የአብዮት ጎዳና ይዘው ለተጋዙትና በመጋዝ ላይ ያሉት ምሁራኖች ግና ጽንሱንም ተግባሩንም ይዘው ከንድፈ-ሐሳቡ (theory) አዋኽደው ነበር። በዚህ ምክንያት ጽንሐተ-ምሁራን የሚል የቅጽል ሥም ተሰጥቶዋቸዋል።

በዚህ አስተሳሰብ ይሆን የኢሕአፓ ድርጅት ትግሉን የማያቆመው እና ዝምም የማይለው? መልሱ አዎንታ ሲሆን እግር በኢትዮጵያ ምላስ በኤርትራ እስቲንቀሳቀሱ ኢሕአፓዊ ትግል ለሰኮንድ እንኳን አያቆምም። እንግዲህ ኢትዮጵያውያንም ሆናችሁ ኤርትራውያን ስለ አመራርም ሆነ ስለ ዴሞክራሲያዊት ኤትዮጵያ የኢሕአፓም አመራር ሆነ የኢሕአፓ ተከታዮች በሚያደርጉት ይሁን በሚናገሩት ላይ ግራ ባይገባን ይሻላል። በትዕግሥት ማየትና ማስተዋል ይገባል እላለሁ። የኢሕአፓ ድርጅት ምን መደረግ እንዳለበት ትክክለኛው ጎዳና በሚል ርዕስ በጥቅምት ፲፪፣ ሺ ዘጠኝ መቶ ስድሳ አምስት በቁጥር 2 አመላክተዋልም አትተዋልም። ጽሁፉን ለማየት ለሚፈልግ ሰው በYaTewlid.com Democracia ይመልከቱ። የዛሬ 41 ዓመት መሆኑ ነው።

በethiox.com ድኅረ-ገጽ በተጣፈ መጣጥፍ (Leadership style unfolds in Eathiopia —dated Jan. 13, 2012) ባጭሩ እንዲህ ይል ነበር። ግንባሮች፣ ነፃ አወጭዎቹ፣ የኤርትራም ሆኑ የትግሬዎች፣ መሪያቸው የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ ብቻ ሳይሆን ሊቀ መንበሩም ይሆናል። ማለትም አንድ ሰው መሆን አለበት ስለነበረ በተግባርም ተተገበረ። የኮሎነል መንግሥቱ ኃ. ማርያም፣ የአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ እና የአቶ ለገሠ ዜናዊ አርአያነት በቂ ይመስለኛል። አምባገነንነት ከዚህ አወቃቀርና አሠራር የመነጨ ነው። የብርሃነ መስቀል ረዳም ኑዛዜ ይሀንኑ አወቃቀር ይደግፋል።

በአንጻሩ ደግሞ የኢሕአፓ ድርጅት የግለሰብ አምባገነን ስለሚሰፍን በዲሞክራሲና በዴሞክራሲያ አገባብ እንዲከናወን ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች ይህ ነው የማይባል መስዋዕት ከፍለዋል እየከፈሉም ይገኛሉ። ከባድ ፈተና ነው። ስለ ኢትዮጵያና ኤርትራ፤ ስለ ዲሞክራሲና ዴሞክራሲያ፤ ስለ ኢሕአፓና፤ኢሕአፓዎች፤ ስለ ነፃነትና አርነት፤ ስለ መገናኛና ግንኙነት ብዙ ብለዋል ብዙ ሠርተዋል። ብዙም ጽፈው አልፈዋል።

አሁንም ቢሆን በቀላሉ አማርኛ “ለብር አብር” በሚል መፎክር ማለትም፤ድልድይና መንገድ  (BR) ጉልቻ (ABR) በሚል ቀመር ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች ሥራቸውን እየሰሩ ናቸው።  በዲሞክራሲና በዴሞክራሲያ ያለው አንድነትና ልዩነት በተምሳሊነት እያሳዩ ናቸውና ኢትዮጵያውያንም ሆናችሁ ኤርትራውያን ብትከታተሉዋቸው ሕዝባችሁን ብቻ ሳይሆን አገራችሁንም ከአንጃበበባት “ችግር” ማርከሻ ለማለቀቅ ይቻላል። ምርጫውም የእኛው ይሆናል። በተሰጠው የአመራር አርዕስት ጉዳይ ሁሉም በቀና መንፈስም ሆነ በጥላቻ ቢወያዩና ቢገናኙ መፍትሔ እንደሚገኝ በእርግጠኝነት መተንበይ ይቻላል ብዬ አምናለሁ። ማስታረቅ፣ ማስፈረድና መደራደር በኢሕአፓ አሠራር ቅደም ተከተል (priority) አለው።

## *ዲሞክራሲና ዴሞክሲያ፣ ልዩነትና አንድነት*

በኤትዮጵያ የአብዮት ፍንዳታ ጊዜ የኮለጅ ምሩቃን ያሰራጩት መስመር በሦስት ይከፈላል። እነሱም የፈረንሳይ፣ የአሜሪካ እና የኤትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎች ነበሩ። የፈረንሳይ መስመር የተከተሉ መኢሶን በተባለ ድርጅት ተጠቃልለው "ዴሞክራሲ በገደብ" በሚል መፎክር እስከ መጨረሻው ተታግለው አለፉ። የአሜሪካን የአብዮት መስመር እንከተላለን ያሉት ደግሞ በኢሕአግ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አንድነት ግንባር) በሚል ሥም ተደራጅተው ኤርትራን አቋርጠው ከበርሊን (በዛን ጊዜ ምዕራብ) ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ሦስተኛው የአብዮት ንድፈ ሐሳብ ተከትሎ በኤትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ትግሉን ሊያራምድ የተነሳሳው አካል ኢሕአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) ተብሎ ተሰየመ። የዚህ ድርጅት ዋና መመሪያው ኤትዮጵያዊ ሲሆን የትግል መሣሪያው ደግሞ ዲሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ ነበር። ይኸም ማለት በኤርትራ ኢሕአፓ የሚል ድርጅት ነበር (አቶ ኢሳያስ በ1998? አፍርሶታል ይባላል)፤ እንደዚሁም በመላው ኤትዮጵያ ትንሽዋ ዲሞክራሲያ እንዲሰራጭ የኢሕአፓ ፕሮግራምና መመሪያ ሆነ።

በፅንሰ-ሐሳብና በንድፈ-ሐሳብ የኢሕአፓ ድርጅት ትክክለኛውን ጎዳና ቀይሶ እያለ በምን ምክንያት ነበር ተቀዋሚ የበዛበት ተብሎ ብዙ ጊዜ ይጠየቃል። መልሱ ከላይ እንዳልኩት ከፈረነሳይና ከአሜሪካ አብዮት የተማሩና ያስገቡት ንድፈ-ሐሳብ ብቻ ሳይሆኑ የትግል ዘዴውም ከየአቅጣጫው ከሶሻሊስት አገሮች ከመጡት ታጋዮች ነን ከሚሉት ለምሳሌ ከሶቪየት፣ ከቻይና፣ ከኩባና እንደዚሁም ከተለያዩ መጽሐፍቶችና መጽሔቶች ያነበቡ ለምሳሌ ከቪየትናም፣ ከአልጀሪያ፣ እና ከካምቦዲያ የመሳሰሉት ትምህረት አግኝተናል በሚል ሰበብ-አስባብ የኤትዮጵያ አብዮት ትክክለኛው ጎዳና ሊሲት ተገደዋል።

የኢሕአፓ የትግል መስመር ለጊዜው እንተወው እና ለመሆኑ የኢሕአፓ *ትክክለኛው እምነትና እሴት ምን ነበር አሁንስ ምን መስመር ይከተላል?* እንደ አንድ መስካሪና የኢሕአፓ ተሚጋች መልሴ በቂ አይሆንም ምላሹ ያለው በአንባቢውና በኤትዮጵያውያን ሕዝብ ይመዘናል። የመመዘኛው በጎሪያት የሚከተሉት ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ።

**አንደኛ**፣ ከፊድዋሊዝም ለመላቀቅ በተደረገው ትግል መሬት ለአራሹ ሆነዋል ወይ? እስከ አሁን ድረስ የግል መሬት ያለው ኢትዮጵያዊም ሆነ ኤርትሪዊ አላውቅም።

**ሁለተኛ**፣ ከአድኀሪ ቢሮክራሲ ለማላቀቅ ተራማጅ ቢሮክራሲ ሰፍነዋል ወይ? መልሱ ከወጣት ኤርትሪያውያን ማግኘት ይሻላል። በኢትዮጵያ ደግሞ የሙስና ስርጭት መከታተል ይጠይቃል።
በሁለቱ አገሮች የኤኮኖሚ ውድቀት አለ መነሻውም አንዱ ለሌቦች ወለል ብሎ በር በመከፈት ሌላኛው ደግሞ ግጥም አድርጎ በር በመዝጋት ወደ ከፍተኛ የሙስና ተግባራት ሰፍነዋል።

ሦስተኛ፣ ከአርነት በስተቀር ባርነት በኢትዮጵያና በኤርትራ እንዳይሰፍን የተካሄደው ትግል አሁን የት እንዳለን ለቀባሪው አረዱት ይሆነብኛል።

በሌላ አነጋገር ምንም ለውጥ የለም ከሆነ ኢሕአፓ የተባለው ድርጅት ትግል መቀጠሉ ሊያስገርም አይገባም ለማለት ነው። የሚያስገርመው ጉዳይ ግና አለ። እሱም የሚከተለው ነው።

ኢሕአፓ እምነቱና አሰራሩ ትክክል ሆኖ እያለ ቢያነስ ለምን በራሱ አባላትና ደጋፊዎች ለማደግ አልቻለም? ሁሌም ችግር አይጠፋውም? አዎ አባባሉ ትክክል ነው። ምክንያቱም ግና እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

አንደኛ፤በኢሕአፓ አመራር ውስጥ አንጃ ተፈጥሮ በሚሊዮን ሊቆጠሩ የሚችሉ አባሎችና ደጋፊዎች አልቀዋል። ታሪክ እያወጣው ስለሆነ እዚህ መድገሙ አይታየኝም። የአንጃ ጉዳይ በወቅቱ ጉዳዩ በይፋ አደባባይ ስለአልወጣ ብቻ እነሆ አሁንም ከእንደገና የሚያገረሽ ይመስላል። የአንጃ ታሪክ የግድያና የሰቆቃ ሁኔታ ስለነበረ ለታሪክ በስተቀር ለትውልድ የሚሆን ቅርስ የለውም። ከሱ ለመማር ከሆነ አሁንም መተማመናችን - TRUST - በኀብረ-ሰባችን ከእንደገና መስፈን አለበት።

ሁለተኛ የኢሕአፓ ውዝግብ ካላይ እንደተገለጠው የግድያ ብቻ ሳይሆን የቀጣዩ የትግል መስመር ነው። ይህም ማለት በዲሞክራሲያ እና በዴሞክራሲያ መካከል የተካሄደና የሚካሄድ ያለ ጉዳይ ነው። ሰሚውን ሕዝብ ከኢሕአፓ ወጭ ያለው ከማስገረምና ከማሳዘን ብዙም አላለፈም። የሚስተካከል ጉዳይ ነው። ስለ ኢሕአፓ ለሁለት መከፈል በ Mahder.com የጣፍኩትን ይመልከቱ፥ አርዕስቱ፥ በእንግሊዝኛ ነበር የተጻፈው እንደሚከተለው EPRP’s Leadership split into two

በአሁኑ ጊዜ ብዙ መጽሐፎች እና ብዙ በድምፅ የተቀዱ ዶክመንቶች ስለአሉ አሁንም በመቀጠል ላይ ስለሆኑ ኤትዮጵያውያን ሀቁንና እውነቱን ስለ አገራችውንና ሕዝባቸው እንዲያውቁ፥ በተለይም በስደት ላይ የሚኖሩ ስለ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች ታሪክ ቢያውቁ፥ ይጠቅማቸዋል ብዬ አስባለሁ።

በቅርቡ የግል memoire/autobiography ወይም biography ታሪክ በማስመሰል ሁለት መጽሐፎች ለንባብና ለገበያ ወጥተዋል ዝናም ያተረፉ ይመስላሉ። እነሱም አንዱ በእንግሊዘኛ -tower in the sky- በሕይወት ተፈራ ሲሆን ሌላው ደግሞ በአማርኛ “የአሲምባ ፍቅር” በካሕሳይ አብርሃ ናቸው።

መጽሐፎቹን ሳላነባቸው የተነገረኝ የግል ማስታወሻ ናቸው ተብሎ ነበር። እኔም በመረጃ መተማመን (በዶክመንተሽን) ከሚሉ ወገን ስለሆንኩ እነዚህ ሁለት መጽሐፎች የሆኑ ለሪፈርንስ ይሆናሉ በሚል በእንግሊዘኛ ድጋፌን ሰጥቻለሁ። በAssimba.org ይመልከቱ።

መጽሐፎቹ በእኔ አስተያየት ለሪፈርንስ ይጠቅማሉ ብየ ነበር የጣፍኩት። አሁን ግና ብዙ ግለ ሰቦች፣ ድርጅቶች እና ድኅረ-ገጾች አቃቂርና ድጋፍ በመስጠት ስለሆኑ የግሌንም አስተያየት ለመስጠት ተገድጀአለሁ።

## የአሲምባ ፍቅር፤ ስለ ፍቅር ወይስ ስለ ነፃነትና አንድነት?

አንድ የብጻይ/comrade ታናሽ ወንድም የመጽሐፉን ርዕስ ሲያይ አሲምባ ደግሞ የምን ፍቅር አለው? ብሎ ድንገት አስደነገጠኝ። እረስቸው ነው እንጂ በአሲምባ ጦርነት ጊዜ (በወያኔና ኢሕአሠ መካከል የተካሄደ) የቆሰለ ጀግና ነው። እስቲ ላንብበውና እንረዳው ምክንያቱም አሲምባ ሲባል ለኔ የመጣልኝ ሕዝቡንና አካባቢውን ነበር። እንደሰማሁትና እንደተረዳሁት የአሲምባ ሕዝብ ከሚገባ ትሁትና የዋህ፡ ጨዋና ተግባቢ እንደሆነና የሚኖርበት አካባቢም ለጤና ተስማሚ መሆኑን ነበር፤ ታዲያ ፍቅሩ ከዚህ የመነጨ መስሎኝ ነበር እንደዚያ ያልኩት። ካነበብኩት በኃላ ግን የጓዴ ወንድም የመጀመሪያው ስሜቱ ልክ ነበር። የጽሑፉና ርዕሱ ዓላማ ፈጽሞ አይገናኙም። አራባና ቆቦ ናቸው።

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አመራር፤ ዲሞክራሲያና ዴሞክራሲያ አብረው ተጣምረው የሚገዙ ናቸው። ተነጣጥለው የሚሄዱ አይደሉም። እንደነ አቶ ካሕሳይ አባባል ከሆነ ኢሕአፓ የጦር ሠራዊት ድርጅት ይመስላል። ኢሕአፓ የፖለቲካ ድርጅት ነበር አሁንም ነው። ነብሱን ይማርና አንድ ተመስገን ፍስሐጽዮን የተባለ የኤርትራ ሚስጢር አዋቂ ነኝ የሚል እንዲህ ብሎኝ ነበር። ቃል በቃል እንደሚከተለው ነበር። “የኢሕአፓ መሪው አውቀውአለሁ፡ ኢሕአፓ 47 ሽጉጥ ሰጥተናቸውን መንግሥት እንዲገለብጡ አዘናቸዋል” ሲለኝ በሳቅ ሞትኩ። የያኔ መልሴ ግና የኢሕአፓን መሪ ካወቅህ ሚሊዮነር ትሆናለህ መሪው ጠፍቶ ይሁን ወይ ባለመኖሩ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ እየታሰረ፣ እየተገደለና እየተሰደደ ነው ብዬ አልኩት። አሁንም ወደ ነበርነበት በመመለስ አቶ ካሕሳይና ወይዘሪት ሕይወት ይኸን የአቶ ተመስገንን ታሪክ ሊደግሙልን የተነሱ ይመስላል። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ። ግና በኤትዮጵያ ታሪክ ራሳን እንደማትደግም እተማመናለሁ። አድኻሪ አባባል ነውና። የአቶ ካሕሳይ እና የወ/ት (አግብተው ከነበሩም ወ/ሮ ጌታቸው) መጥሐፍች እንደሚተርኩት ኢሕአፓ የፍቅር (ፍትወተ-ሥጋ) ድረጅት አልነበረም ሊሆንም አይገባውም።

## አቶ ካሕሳይ

ፍቅር የሚለው አቶ ካሕሣይ በእሱና በአቶ ይመር ንጉሤ ከዛም አልፎ ከአቶ ይመር ቤተሰብ ከሆነ ምንም ተቃውሞ ወይም አስተያየት የለኝም፤ ሁላችን በግላችን የምናደርገው ባህላችን ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ ተፎጥራችን ስለሚያስገደደንም ጭምር ነው። በዚህ ተግባሩ ሊደነቅ ይገባዋል።

ሆኖም ግን ስለ መጽሐፉ ይዞታ ያለኝ አስተያየት እንደሚከተለው በአራት ነጥብ አስቀምጣለሁ።

- ስለ ጦርነቶች

ስለ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች አቶ ካሕሳይ አደባልቆ ሲጽፍ በጣም ያሳዝናል እንኳንስ ተደባልቆ ለየብቻውም አስቸጋሪ ነበር። ነውም። ጦርነት ማለት ለኢሕአፓና ኢሕአፓዎች ትግል ለማለት መሆኑን (አማኑኤል) መገንዘብ ነበረበት።

ዋናው የኢሕአፓ መፎክር ሠላም፣ በኤርትራ፣ ዴሞክራሲያ በኢትዮጵያ የሚል እንደነበር ማንም አይስተውም ነበር። የኢሕአፓና የኢሕአፓዎች መተማመኛ ቃል TRUST ባይሆን ኖሮ ከመኻልና ከደቡብ ኤትዮጵያ ወደ ካሕሳይ ትግሪኛ ተናጋሪ አገር ባልጎረፉ ነበር። እንደዚሁም የአየር ወለድ ቡድን ( በነገራችን ላይ ለምን ስማቸው በመጽሐፉ እንዳሰፈራቸው አይገባኝም፤ ቅንነት የጎደለው ይመስላል አለበለዚያ የአባታቸው ሥምም ጨምሮ ማሳተም በተገባው ነበር። የኤትዮጵያ ጉዳይ በሠላምና በዴሞክራሲያ ይፈታል ብሎ የኢሕአፓ ድርጅትና ኢሕአፓዎች ባያሳምነዋቸው ኖሮ ወደ አሲምባ ባልሄዱ ነበር።

ይህን ሀቅ ሁኔታዎችና እምነቶች በውስጡ ተቀብሎ ሲያበቃ አቶ አማኑኤል በማያስፈልግ አታካሪ እየገባ ሠራዊቱንና አመራሩን አራበሸው። ለምሳሌ አበራ ጣሰውና አብደላ በሚላቸው መካከል አለመተማመን እየፈጠረ፣ ወ/ሮ ሰላማዊት በሰላማዊ መንገድ ልታዝናናው ብትሞክር እምነተ-ቢስ ስለሆነ በገዛ እጁ ተፍረከረከ። ዋናው ቁም ነገሩ አማኑኤል የኢሕአፓን ተልእኾና ዓላማ እስከ አሁን ድረስ አልገባውም ለማለት አያስችለኝም። ባይፈልግና የተለየ ዓላማና መንገድ ቢኖረው ነው ብዬ አስባለሁ። ካልሆነም ቀለል ባለ አማርኛ ወይም ትግሪኛ "አማኑኤል ሜዳ እያለ ከአመራር ወገን፣ ከወታደራዊ ወገን፣ ከፖለቲካዊ ወገን፣ እምነትዬና የሥራ ምድቤ ብሎ ይነገረንና በዚሁ አርዕስት ጉዳይ ለመረዳዳት እንችል ነበር። እኔ እንደገባኝ ከሆነ አቶ አማኑኤል ራሱን የአመራር ዘበኛ (body guard) አድርጎ ስለ ቆጠረ የኢሕአፓ አመራር ደግሞ ዘበኛ ስለማያስፈልጋቸው ነገሩ ግራ የገባው መሰለኝ። አመራሮቹ ግና አቶ አማኑኤልን በተለያዩ የሥራ መስክ ሥልጠና እየሰጡት መሆኑን አልገባውም ነበር ለማለት ይቻላል። ምናልባትም ቀናነቱንና ታታሪነቱን ተገንዝበው ለመከላከሊያ ሚኒስትር ወይንም ለጀኔራልነት አጭተውት ይሆናል። አለበለዚያ እነዚህ ቆንጥሮ የጠቀሳቸው ጽንሐተ-ምሁራን እንዴት ሊያቀርቡት ቻሉ? ሞተዋልና መመስከር አይችሉም ብሎ ለአንባቢዎች እየዋሸን ከሆነስ? እንደ አማኑኤል አባባል ደብተራው ለፖርቲ አባለነት ታጭተሃል ብሎኛል። እንዲያውም አቶ አማኑኤል ሲጽፍ እንዲህ ይላል በ (ገጽ 375) "በለሳን ዋና የጦር ሰፈር ለማድረግ ስለታሰበ ነው ለዚህ ተልእኮ የፈለግንህ" አለኝ ደብተራው።ይህ አባባል ከደብተራው እምነትም ሆነ የሥራ ድርሻው ምንም አይገናኝም። ደብተራው ብሎ የጦር ሠፈር መስራች፤ የጦር ሠፈር ያፈረሳል እንጂ። የደብተራው ጦር ሠፈር ጭንቀላቱና ልቡ ነው። መሣሪያውም ብዕርና ወረቀት ነበር አቶ አማኑኤል አሁንም በማስገረም በገጽ 375 ለማስታወሻ ደብተራው ጠመንጃውን መረቀልኝ ይለናል። ወዮ ጉድ።

ትዝታዎች (memoire) የግል ታሪክ (autobiography) የሌላ ሰው ታሪክ (biography) ሦስቱን አቶ አማኑኤል ሊያጎርሰን ይፈልጋል። በኢሕአፓና በወክንድ የተዘጋጀ በአል ላይ በከፍተኛ ደረጃ የተሸጠው መጽሐፍ የአሲምባ ፍቅር ነበር። አርዕስቱን አይተን ገዛነው እንጂ ይዘቱን መርምረን አልነበረም። በአንፃሩ የግል ማኅደር ብሎ የደረሰው የአቶ መኮንን አርአያ ሁለት ሀባ ብቻ ነው የተሸጠው። ለምን ቢባል በማስመሰል ለገበያ ተቀነባብሮ የተዘጋጀ አልነበረምና ነው። በነገራችን ላይ እስከ ዛሬ ድረስ በኢሕአፓ ሰዎች የግል ታሪካቸውን የከተቡ አቶ መኮንን አርአያ ናቸው። የመጽሐፉ አርዕስት - Negotiating a lion's share of freedom - ይላል።

- ## ስለ ደብተራው

ምንም እንኳ (ACE) ደብተራው አንስተህ ብታፈርጠውም የተከታዮቹ ዕምነት፣ ጽናትና ዓላማ ፍንክች አይልም። ደብተራው "ሽጉጥ አጥፍቶ ከተማውን አተራመስነው።" የምትለዋ አባባል የተለየ መልዕክት ያላት ትመስላለች። ካተራመሳችሁ እንኳ ደብተራው ሆን ብሎ በእናንተ ሊደረግ የሚፈልገው ተልዕኮ ቢኖር ነው እላለሁ። ለገጠር ሰዎች የከተማ ሥራ (ፍተሻ) መስጠቱ ሊሆን ይችላል። እኔ የማውቀው ደብተራ የብዕርና የወረቀት ሰው ስለሆነ የሽጉጡን ጉዳይ አለ ቦታው ተነስተዋል።

ደብተራው ሰውን በማይጎዳ መንገድ ብዙ ሰዎችን ሊያሳስት ይችላል። ለምሳሌ አማኑአል ስለ ደብተራው ትግሪኛ አለማወቅ ሲጽፍ "አገር ቂጥ ለማለት መዓኮር አለ" ይለናል። ደብተራው አይደለም ትግሪኛ የወፍ ቋንቋ ይቅርና የሰይጣን ቋንቋ የሆነው ግዕዝ ያውቃል። መዓኮርማ የመሳቂያና የመሳለቂያ ቋንቋው ነበረችና ነው።

እንኳን አቶ ካሕሳይ ስለ ደብተራው የሽጉጥ አጠቃቀም ሊያውቅ ቀርቶ አቶ መርሻ ዮሴፍ -የትንሽዋ ዲ መሪ - ሳይቀር ስለ ደብተራው እንዲህ ብሎኝ ነበር። ወቅቱ በጎንደር ክፈለ ሀገር ኢሕአሠን ከቦ ለመያዝ በተደረገው ዘመቻ አቶ መርሻ መርዶውን ሲነገረኝ ቃል በቃል እንዲህ ነበር ያለኝ "ደብተራው ደግሞ እኮ ሽጉጥ ነበረው" እኔ ምንም አላልኩትም ምክንያቱም ደብተራው እንደሚሰወር አውቃለሁና። በተደጋጋሚ በንጉሣዊም ሆነ በደርጋዊ መንግሥታት አድርጎታልና። አሁንስ ደብተራው የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው አለ? የዚህ ጥያቄ መልስ ጥቅም ይገኝበታል ሚሎዮነር ያደርጋል ከተባለ እርግጠኛ ነኝ ሬሳውን አገኝቸዋለሁ በማለት እንደሚረባረቡ አልጠራጠርም። ደብተራው ግና የደርጅቱ የኢሕአፓ ዓላማና ግብ ሲጠናቀቅ ብቅ ማለቱ አይቀሬ ነው። ያኔ የአቃቂረኛው ጌታቸው ረዳ "ደብተራው የት ደረሰ?" ምላሽ ያገኛል። አቶ ካሕሣይ ደብተራው በሚገባ መክሮህ ነበር ምክሮችም ለሌሎች ይጠቅማሉ በማለት ከዚህ በታች እዘረዝራቸውአለሁ።

1. በእኔ በኩል ችግር የለም። ነገር ግን ሁልጊዜ ሐቅ መናገር አያዋጣም (ገጽ 107)
2. "አማኑኤል" ጓደኛና ድርጅት ለያይተህ ዕወቅ ብሎ መክሮኛል
3. ደግሞስ ማን ማንን ይቀጣል (ሒስና ግለ-ሒስ እያለ ለማለት)
4. እኛ ስንፈራ ደብተራው በእኛ ምትክ መርፌ ይወጋልን ነበር (guinea pig) እንዲሉ (ገጽ 60)

- ## ስለ ፍቅር

አቶ "አማኑኤል" የሚል ሥም ማን እንዳወጣለት እንጃ እንጂ ደብተራው አወጣልኛ ብሎ ስሜ "ነብዩ" ይባላል ብሎ የተዋወቀኝ ሰው አለ። አማኑአል በሠማይ ቤት ጥሩ ነገር ቢሆንም ቅሉ በአዲስ አበባ ከተማ ግና ሥም አይሆንም። ምን ያደርጋል አቶ ካሕሳይ በዚያን ጊዜ የባላገር ሰው ነበሩ።

ለማነኛውም አቶ ከሕሳይ የፍቅር ሰው ከሆኑ የአሲምባ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ እንዴት እንደሚኖርና እንዴት እንደሚንቀሳቀስ፣ የተታገላችሁለት የነፃነት ጮራ አገኘ ወይስ

ተነፈገ? ባልደረቦችህ ማለት የትግል ጓደኞችህ በተለይም በወሎ ተይዘው የተረሸኑ ሥማቸውን በመጽሐፍህ ለዛውም ያለተማላ ሥም ማስፈርህ ባሻገር ወላጆቻቸው የት ደረሱ ብለህ አስበሐል? በምን ልርዳቸው? በምን ላጽናናቸው? ባጠቃላይ ኢ.ሕ.አ.ፓና ኢ.ሕ.አ.ፓዎች የተረሸኑበት፣ የተሰዉለት፣ የታሰሩለት፣ የተሰደዱለትና ገና ሊሰዉለት የሚታገሉ የፖለቲካ ሥርአት እንዴት ነው የሚሳካው ብሎ አስቦበት ይሆን?

አቶ ካሕሳይ ነብስህን ያዳኑ ቤተ-ሰብ ስትረዳቸው፣ ፍቅረኛህ ድላይ ቤተ-ሰብ የላት ይሆን? አንዲት ልጅ መጽሐፍኽን አንብባ እንዴት ነው ብለው ሲጠይቁዋት እንዲህ ብላ መለሰች። "ምን ዓይነት ጨካኝ ሰው ነው፣ እንዴት ፍቅረኛውን ጥሎ ይሄዳል፤ ደግሞ የፍቅር መጽሐፍ ብሎ መሰየሙ" ብላ ተናገረች። እንግዲህ የአቶ አማኑኤል የአሲምባ ፍቅር አርዕስት ተምታታ/ተኮላሸ ማለት ነው።

- ከድርጅት ስለ መሰናበት

አማኑኤል በሰጠው ምክንያት ኢ.ሕ.አ.ፓ በስትራተጂያዊና በጦር ስለተሸነፈና … ስለ ወደቀ ወጥቸ ሄጃለሁ። በዚህ አባባልህ እንኳ እንዳትፀና እኔ ብቻ አይደለሁም የሸሸሁት ሌሎች 75 እና ብርሀኑ ነጋም አለበት ስትል የባሰውን ኀሊናህን ሸጥከው። ይሁን እሺ ስለ ስትራተጂ አልገባህም ልበል፣ ግና ስለ ኀሊናው አማኑኤል አያውቅም ነበር ለማለት ይከብደኛል። ልብ ብሎ ላስተዋለው ሰው አማኑኤል ታማኝ እንዳልነበረ ራሱ ገልጸ ጽፈዋል። በእጁ ሊያደርስ የተሰጠው የአደራ ደብዳቤ ከፍቶ ማንበቡን ገልጦልናል። ከዚህ የባሰ የዕምነት ማጉደል ምን አለ? ለትምህርት እንዲሆንህ አሁንም የአሜሪካን የፖስታ ቤት ሙዚየም ሄደህ ተማር። ያዳነህን ሰው የመጽሐፍ ዋና ቀስቃሽ ኢላማ አድርገህ የኢ.ሕ.አ.ፓ የተቀደሰ ታሪክ አረከስከው። የሚያሳዝነው ከአሜሪካ ተኪዶ በማይጨው ተዋናይ ስትሆን ነው። ልበ-ወለድ ይሉሃል ይህ ነው።

አቶ ካሕሣይ ከዚህ በፊት አቶ ይማም የተባሉ ታጋይ የኢ.ሕ.አ.ፓ መሪዎችን ለማግኘት ያልገቡበት ቦታና ያልቆፈሩት ጉድጋድ የለም። ሆኖም ሳይሳካላቸው ቀርቶ እንደአንተው ስሜታዊ የሆነ መጽሐፍ ጻፉ። የመጽሐፉ አርእስትም "Yankee, Go Home" ሆኖ በሚያስፈራራ የመጽሐፍ ሽፋን 'ተከሸኖ' ኢ.ሕ.አ.ፓን ሽብርተኛ ድርጅት ለማስባል ለገበያ ወጥተዋል። ምን ያህል ገበያ እንዳገኘ አላውቅም። የመጽሐፉ ሽፋን ግን እንኳን ለኛ ኤትዮጵያውያን የጦር መሣሪያ ለማናመርት ለአሜሪካውያን ጭምር ማለት መሣሪያ ለሚያፈቅሩ በአሁኑ ሰዓት ያስፈራል።

በእኔ አመለካከት (call me by my name ነውና) ባጭሩ የመጽሐፉ ሽፋን እንደሚናገረው

# የአሲምባ ፍቅር

## ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ነፃነትና ዲሞክራሲ በተደረገ ሕዝባዊ ትግል ላይ ተመሠረተ እውነተኛ ታሪክ

## ከካሕሳይ አብርሃ ብሥራት

አንባቢ ሊረዳው እንደሚችል እርግጠኛ ባልሆንም ምክንያቱም የተራራዎች ፎቶግራፍ በመጽሐፉ ርዕስና በደራሲው ሥም መካከል ይገኝበታል። በእኔ አተረጎገም ግና እንደሚከተለው ይሆናል።

**የዴሞክራሲያና የሠላም ፍቅር**
**አለቀ ደቀቀ - ታሪክ ሆነ**
**ጉዳዩም፤**
**ካሣውም፤**
**ክፍያውም፤ሆነ**
**ቂም ብቀላው**
**በከሳቴ ብርሃን ተከናወነ።**

ለማነኛውም ፍርሃት የሚባል በኅብረተ-ሰቡ ባይሰፍን ኖሮ አቶ አማኑኤል ሁሉንም በቀላሉ ይረዱት ነበር። አሁንም ስለፈሩ ነው የወያኔን አቅዋምና ትርምስ በባላገርም ሆነ በከተማ ትንፍሽ ያላሉ። ነፃነት ለሁላችንም ጠቃሚ ነው። ፍርሃትዎን አስወግደው ሌላ መጽሐፍ እንዲጽፉ እጠይቆታለሁ። ባለ ታሪክ ኖትና፤ ታሪክ ሲባል ደግሞ ከሺ በላይ ነው።

### *የወት ሕይወት ከኅዳር ፳ ቀን ፪ሺህ ፩ ዓ.ም heroism or patriotism?*

በጭሩ የይሕወት መጽሐፍ በእኔ አስተያት "ከአስተማሪው ተማሪው በለጠ" ብዬ ደምደሜዋለሁ። ከዚህ በተረፈ የብረሃነ መስቀል ረዳ የምርምራ ቃል ካነበብኩ በኃላ በሁለቱም ጓዶች(ባል/ሚስት) አስተያየቴን እሰጣለሁ። እስከዛው አመሰግናለሁ።

### *መደምደሚያ*

የጦርነት ትግል ቀላል ባይሆንም የአብዮት ገድል ደግሞ የበለጠ ከባድ ነው። አቶ ካሕሣይና መሰሎቹ በሚያውቁት ተግባር ቢጽፉና ቢመሰክሩ መልካም ነበር። አለበለዚያ መልካም ሥራቸው ወደ ውሸት ይቀየራል። ውሸትና ቅጥፈት ደግሞ ለሁሉም ጎጂ ነው።

አሁንም ስጋቴ ወደኃላ ተመልሰን ዳግማዊ እልቂት እንዳናስከትል ነው። በሰከነ አዕምሮ ብንመራመር ይሻላል። መረጃዎች አሉ በዶክመንት ዓይነት በዓይነት እየተጻፉና እየተነገሩ ናቸው። ሁሉም የድርሻውን ይጻፍ ይናገር። ሳንሱር ይቅር፣ መተማመን ከእንደገና ይስፈን። መወያየትና መገናኘት ይደረግ። መስመራችንና እምነታችን በሒስና ግለ-ሒስ ይከናወናል፤ የኤርትራ አርነትና የኢትዮጵያ ነፃነት ብሎም የኤትዮጵያ አርነትና/ነፃነት (INDEPENDENCE) በአንድ ጋር ናቸው። ተነጣጠለው አይታዩም። አንድና አንድ ናቸው።